የመጽሀፍ ቅዱስ መበረዝና ኢስላማዊ እይታው

እውን እስልምና ቀደምት መለኮታዊ መጽሀፍት መበረዛቸውን አያስተምርም?

የሕያ ኢብኑ ኑህ

የመጽሀፍ ቅዱስ መበረዝና ኢስላማዊ እይታው

ረቂቅ/Abstract/

ይህ ጹሁፍ በዋናነት የሚያጠነጥነው በመጽሀፍ ቅዱስ መበረዝ ዙሪያ ኢስላማዊ ምንጮች ምን ይላሉ የሚለውን አጀንዳ መሰረት አድርጎ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ክርስቲያኖችና አይሁዶች «መጽሀፋችን መበረዙን ኢስላም አያስተምርም» የሚለውን ገለጻቸውን በመፈተሽ ከመረጃ ጋር ሀሰትነቱን ያሳያል፡፡

ጹሁፉ በሁለት ክፍል የሚቀርብ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የቁርዓን፤ የሀዲስና የከፊል ሰሀባዎችን (የነብዩ (ሰዐወ) ባልደረቦች) መሰረት አድርጎ የሚቀርብ ሲሆን ሁለተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ ቀሪ ሰሀባዎችንና የሙስሊም ሊቃውንትን ትንታኔዎች አካቶ ይጠናቀቃል፡፡

በዚህ ጹሁፍ ከምንም በላይ ትክክለኛውን ኢስላማዊ አመለካከት ለማቅረብ ጥረት ያደረግኩ ሲሆን ትክክል ከሆንኩ ከአላህ እርዳታ ነው፤ ስህተት ከሆንኩ ከነፍስያየና ከሸይጧን ነው። ባጠፋሁት ይምረኝ ዘንድ ልክ በሆንኩበትም ኢኽላሱን ይሰጠኝ ዘንድ እማጸነዋለሁ።

1- መግቢያ/Introduction/

የክርስቲያን ሚሽነሪዎች ደጋግመው ከሚያነሷቸው መከራከሪያዎች ውስጥ አንዱ «ቁርዓን መጽሀፍ ቅዱስን እውነተኛ ይለዋል» የሚለው ሲሆን ተያይዞ ደግሞ የሚቀርበው «መጽሀፍ ቅዱስ ስለ መበረዙ ቁርዓንም ሆነ ሀዲስ እንዲሁም ኢስላማዊ ምንጮች የሚሰጡት ፍንጭ የለም» የሚለው ነው።

የመጀመሪያውን አስመልክቶ መጽሀፍ ቅዱስ ትክክለኛ ለመሆኑ ኢስላም ይናገራል የሚለው (በርግጥ የትኛው መጽሀፍ ቅዱስ ለማለት እንደፈለጉ አይታወቅም የአርቶዶክስ 80 አሀዱ አልያም የካቶሊኮች 73 ወይንም የፕሮቴስታንቶች 66 መጽሀፍ የትኛውን እንደሆነ አይታወቅም ይህ

የሚወሰነው እንደምትወያዩት ሰው ማንነት ነው) የተሳሳተ ምልከታ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በአንድ ወቅት «መጽሀፍ ቅዱስ» የተባለ ጥራዝ እንደነበርና ከጊዜያት በኋላ እንደተበረዘ እንደምናምን ያስባሉ ይህ ግን የተሳሳተ አረዳድ ነው፡፡ ቁርዓን ከጅማሮው «መጽሀፍ ቅዱስ» ስለሚባለው ጥራዝ አያወራም፡፡ የቆሮንቶስ፤ የሮሜ ወዘተ የሚባሉ ኦሪጅናል መለኮታዊ መጽሀፍት ኖረው ኋላ ተበረዙ የሚል እምነት የለንም፤ መጀመሪያውኑ እነዚህ መጽሀፍት የግለሰብ ድርሳናት እንጅ መለኮታዊ አልነበሩም፤ ተያይዞ የሚነሳው «ታዲያ በየትኞቹ ነው የምታምኑት» የሚለው ነው፡፡

እኛ ሙስሊሞች ለሙሳ በወረደለት ተውራት (ኦሪት)፤ለዳውድ በወረደለት ዘቡር (መዝሙር) እንዲሁም ለኢሳ በተወረደለት ኢንጅል (ወንጌል) እናምናለን፡፡ እነዚህ መለኮታዊ መጽሀፍት አሁን ክርስቲያኖች «መጽሀፍ ቅዱስ» ብለው በሰየሙት መጽሀፍ ውስጥ ያካተቷቸው ቢሆንም ኦሪጅናልነታቸውን አጥተው የሰው እጅ ገብቶባቸዋል፡፡ ጥቂት ከብረዛ የተረፉ መለኮታዊ ቅሪቶች ቢኖሩም በይዘት ደረጃ ግን ጥቅል በሚባል አገላለጽ የተበረዙ ናቸው፡፡

ከዚህ በታች ኢስላም እነዚህ መጽሀፍት ስለመበረዛቸው እንዴት እንዳስተማረ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

2- የአረብኛ «ተህሪፍ» አገላለጽ

ይህ ተህሪፍ የሚለው ቃል ቁርዓን ውስጥ በይበልጥ አይሁዶችና ክርስቲያኖች መጽሀፋቸውን እንደበረዙ በሚያትቱ ቦታዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ «ተህሪፍ» የሚለው ቃል «ብዕርን በመጠቀም አንድን ቃል ወደ ሆነ አቅጣጫ ማዘመም (መቀየር)» እንዲሁም «ለራስ ስሜት በሚመች መልኩ ቃላትን መጠምዘዝ» የሚሉ ፍቾዎች አሉት፡፡ (አረጊብ አለኢስፈሂኒ፣ አልሙፋራዳት ፊ ገሪቢል ቁርዓን ጥራዝ 1 ገጽ 122)

በተመሳሳይ አሸህራሳታኒ ስለተህሪፍ ምንነት ሲገልጹ «የተጻፈን ቃል የተዛባ ትርጉም ይሰጥ ዘንድ መቀየር» በሚል ያስቀምጡታል፡፡ ይህን አገላለጽ ሸይሁል ኢስላም ኢብን ተይሚያ እቅቲዳአ ሲራጠል ሙስተቂም ሙኻለፈት አስሀበል ጃሂም ገጽ 8 ላይ በመግለፅ ይጋሩታል፡፡

ይህንኑ ኢብን ተይሚያ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ

«በቋንቋ ደረጃ - መለወጥ ወይንም ማዛባት የሚል ፍቺ ሲኖረው ቴክኒካል ፍችው ደግሞ ጹሁፍን በቃልም ይሁን በትርጉም ደረጃ መቀየር የሚል ነው» (Shaikh ul-Islaam Ibn Taymiyyah, Creed of Hamawiyyah - Chapter 3: The Way of Ahl us-Sunnah Concerning Allaah's Attributes

ስለዚህም በዚህ ተህሪፍ በሚለው አገላለጽ ቁርዓን በግልጽ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ቅዱሳን መጽሀፍትን በጹሁፍ ደረጃ ሳይቀር መልእክታቸውን ያዛቡ እንደነበር ጠቁሞናል። ይህን አስመልክቶ የኢማሙ ማሊክን ሙወጣዕ በተነተነበት ድርሳኑ አልባጂ እንዲህ ያብራራዋል።

« እነሱ (አይሁዶች) ቃላትን አላህ ካስቀመጠበት ቦታ ውጭ ይለውጡ ነበር በዚህም አሰላሙ አለይኩም (ሰላም በናንተ ላይ ይሁን) ማለት ሲገባቸው አሳሙ አለይኩም (ሞት በናንተ ላይ

ይሁን) ይሉ ነበር» አል ሙንተቃ ሸርህ ሙወጣዕ ማሊክ፣ ኪታብ አል ጀሚዕ ባብ ማጃዕ ፊ አሰላም አለል የሁዲ ወነሰራኒ ለሀዲስ ቁጥር 1514 የተሠጠው ማብራሪያ

አል ባጂ በዚህ ማብራሪያቸው እንደሚገልጹት አይሁዶች «አሰላሙ አለይኩም» በሚለው ፈንታ «አሳሙ አለይኩም» የሚለውን ቃል በመጠቀም ትርጉሙን ብቻ ሳይሆን ቃሉንም ይቀይሩ እንደነበር ነው፡፡ ከዚህም እንደምንረዳው ይቀይሩ የነበሩት ትርጓሜ ብቻ ሳይሆን ቃልንም ጭምር እንደሆነ ነው፡፡

ለመግቢያ ይህንን ካልን ወደ እስላማዊ ምንጮች ጠለቅ ብለን ዝርዝር ጉዳዩን ደግሞ እንዳስስ

3- መረጃ ከቁርዓን

የመጽሀፉ ባልተቤቶች መጽሀፍቶቻቸውን አንደሚበርዙ የሚገልጹ የቁርዓን አንቀጾች ብዙ ቢሆኑም ለማሳያነት በዚህ ጹሁፍ ሁለቶችን ነቅሰን አንመለከታለን፡፡

-

✔ 3.1 የመጀመሪያው ማስረጃ የሱረቱል በቀራህ 2:79 አንቀጽ ሲሆን እንዲህ ይነበባል፡፡

هَٰذَا يَقُولُونَ ثُمَّ بِأَيْدِيهِمْ الْكِتَابَ يَكْتُبُونَ لِّلَّذِينَ فَوَيْلٌ مِّمَّا لَّهُم فَوَيْلٌ ۖ قَلِيلًا ثَمَنًا بِهِ لِيَشْتَرُوا اللَّهِ عِندِ مِنْ [٢:٧٩] سِبُونَيَكْ مِّمَّا لَّهُم وَوَيْلٌ أَيْدِيهِمْ كَتَبَتْ

«ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው፡፡ ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው፡፡ ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው፡፡» 2:79

ይህ አንቀጽ በግልጽ ቋንቋ አይሁዶቹ የሆነን መጽሀፍ ጽፈው «ይሕ ከአላህ ዘንድ ነው» ብለው መናገራቸውን ጠቅሶ ያወግዛል፡፡ አንቀጹ ግልጽ የሆነ ጹህፉዊ ብርዘትን/Textual Corruption/ እንደሚገልጽ ማብራሪያ አያሻውም፡፡

አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ አንቀጽ ሲቀርብላቸው አንቀጹ ሁሉንም አይሁዶች የሚመለከት ሳይሆን ጥቂት አይሁዶችን ብቻ ግብ ያደረገ መልዕክት እንደሆነ ቁርዓን አጣቅሰው ለመሞገት ይሞክራሉ:: የሚያቀርቧቸው የቁርዓን አንቀጾችም

يَتْلُونَ قَائِمَةٌ أُمَّةٌ الْكِتَابِ أَهْلِ مِّنْ ۗ سَوَاءً لَيْسُوا يَسْجُدُونَ وَهُمْ اللَّيْلِ آنَاءَ اللَّهِ آيَاتِ [٣:١١٣]

«(የመጽሐፉ ሰዎች ሁሉ) እኩል አይደሉም:: ከመጽሐፉ ሰዎች ቀጥ ያሉ በሌሊት ሰዓቶች እነርሱ የሚሰግዱ ኾነው የአላህን አንቀጾች የሚያነቡ ሕዝቦች አሉ::» 3፡113

إِلَيْكُمْ أُنزِلَ وَمَا بِاللَّهِ يُؤْمِنُ لَمَن الْكِتَابِ أَهْلِ مِنْ وَإِنَّ اللَّهِ بِآيَاتِ يَشْتَرُونَ لَا لِلَّهِ خَاشِعِينَ إِلَيْهِمْ أُنزِلَ وَمَا اللَّهَ إِنَّ ۗ رَبِّهِمْ عِندَ أَجْرُهُمْ لَهُمْ أُولَٰئِكَ ۗ قَلِيلًا ثَمَنًا الْحِسَابِ سَرِيعُ [٣:١٩٩]

«ከመጽሐፉም ባለቤቶች ለአላህ ፈሪዎች በአላህ አንቀጾችም ጥቂትን ዋጋ የማይለወጡ ሲኾኑ

በአላህና በዚያ ወደ እናንተ በተወረደው በዚያም ወደእነርሱ በተወረደው የሚያምኑ ሰዎች አልሉ። እነዚያ ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው። አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።» 3፡199

የመጀመሪያው አንቀጽ የሚያወራው በነብዩ ሙሀመድ (ሰዐወ) ስላመኑ አይሁዳውያን ሲሆን እነዚህ አይሁዳውያን በቁርዓን አምነው ሌሊት የሚያነቡ ህዝቦች ናቸው (ተፍሲር ኢብን ከሲር ለአንቀጹ የሰጡት ማብራሪያ)

በተመሳሳይ ሁለተኛው የቁርዓን አንቀጽ የሚያወራው በነብዩ ሙሀመድ (ሰዐወ) ነብይነት ስላመኑ አይሁዳውያን ሲሆን እነዚህ አይሁዳውያን በመጽሀፋቸው ውስጥ ስለ ነብይነታቸው የተገለጹ እውነታዎችን ለቁሳዊ ጥቅም ብለው የሚደብቁ ያልሆኑ እውነተኛ አማኞች ናቸው (ተፍሲር ኢብን ከሲር እንዲሁም ተፍሲር ጀላለይን ለአንቀጹ የሰጡትን ማብራሪያ)

ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን ግልጽ መሆን ያለበት በዚህ የብረዛ ተግባር ላይ አይሁዶችና ክርስቲያኖች

እንደተሳተፉ ሲገልጽ ሁሉም የአለማችን አይሁድና ክርስቲያን ተሰባስቦ ፈጽሞታል ማለት ግን አይደለም፡፡ ነገር ግን ለዚህ ሀላፍትና የወሰዱ ሰዎች(ሊቃውንት) ተግባሩን ከፈጸሙትና መጽሀፉን ካዛቡት አማኙም በጭፍን እየተከተለ ነውና በእጃቸው ያለው መጽሀፍ እንደተበረዘ ይህንን እራሳቸው እንደፈጸሙት ጥቅል በሆነ መልኩ ይገለጻል (ይህንን አስመልከቶ ዝርዝሩን ወደ ኋላ የኢብን አባስን ተፍሲር ስናስቀመጥ በስፋት እንመለከተዋለን)

ስለዚህም ከነዚህ ማስረጃዎች የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ እንችላለን፡፡

1- ቁርዓን በግልጽ ቋንቋ አይሁዶች በእጆቻቸው መጽሀፍ ይጽፉ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

2- በተጨማሪም አይሁዶች «መጽሀፍን» በእጆቻቸው ከጻፉ በኋላ «ይህ ከአላህ ነው» ይሉ ነበር፡፡

3- አንዳንድ ሰዎች አይሁዳውያኑ መጽሀፍ በእጆቻቸው እየጻፉ ይህ ከአምላክ ነው የሚሉት መጽሀፍ ቅዱስን ሳይሆን ታልሙዳቸውን ነው ሲሉ ይከራከራሉ ይህ ግን የሚያስኬድ አይደለም ምክንያቱም አይሁዳውያን በየትኛውም ጊዜያት ታልሙድ የአምላክ ቃል ነው ብለው አያውቁም። ይህንን አስመልክቶ እውቁ የታልሙድ ምሁር ራቸሜል ፈሬይድላንድ እንዲህ ይላል

« እኛ (አይሁዶች) ታለሙድ በሩዋች ሀ ኩዳሽ (መንፈስ ቅዱስ) መሪነት የተጻፈ ነው ብለን አናምንም። ታልሙድም እራሱ የአምላክ ቃል ነኝ አይልም ከዛ ይልቅ ታለሙድ የቶራህ (ኦሪት) ማብራሪያና ትርጓሜ ነው።»

http://therefinersfire.org/talmud_proves_messiah.htm+jews+claim+the+talmud+is+from+god&hl=en&ct=clnk&cd=10&gl=ae)

በመጨረሻም አጉቀጹ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው የሚያወራው ስለአይሁዳውያን መለኮታዊ መጽሀፍት መበረዝ ነው (ኦሪትንና ዘቡርን ስለያዘው ብሉይ ኪዳን)

✔ 3.2 ቁርዓን 4፡157

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል

رَسُولَ مَرْيَمَ ابْنَ عِيسَى الْمَسِيحَ قَتَلْنَا إِنَّا وَقَوْلِهِمْ» وَإِنَّ ۚ لَهُمْ شُبِّهَ وَلَٰكِن صَلَبُوهُ وَمَا قَتَلُوهُ وَمَا اللَّهِ عِلْمٍ مِنْ بِهِ لَهُم مَا ۚ مِّنْهُ شَكٍّ لَفِي فِيهِ اخْتَلَفُوا الَّذِينَ يَقِينًا قَتَلُوهُ وَمَا ۚ الظَّنِّ اتِّبَاعَ إِلَّا [٤:١٥٧]

«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን» በማለታቸውም (ረገምናቸው)። አልገደሉትም አልሰቀሉትምም። ግን ለእነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ። እነዚያም በእርሱ ነገር የተለያዩት ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም።» 4፡157

አንቀጹ በግልጽ እንደሚነግረን ስቅለትን አስመልክቶ ክርስቲያኖች የያዙት አቋም የተዛባና በጥርጣሬ የታጀበ ነው። ክርስቲያኖች ደግሞ

ለዚህ እሳቤያቸው መረጃ የሆኗቸው የወንጌል አናቅጾች ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ ፍጹም ስህተትና የተበረዘ አመለካከት እንደሆነ ቁርአን ግልጽ በሆነ መንገድ አስቀመጠ፡፡

ከዚህ በቀላሉ የምንወስዳቸው ቁምነገሮች

ነ- የስቅለት ጽንሰ ሀሳብ ትክክል ያልሆነ አመለካከት እንደሆነ

2- ክርስቲያኖች ስቅለትን አስመልክቶ ማስረጃቸው በእጃቸው ያሉ ወንጌሎች ሲሆኑ እነዚህ አመለካከቶች ስህተት እንደሆኑ ቁርዓን ገለጸ ማለት በተዘዋዋሪ ለስቅለት የሚቀርቡ የወንጌል አንጾች የተበረዙና ትክክል አለመሆናቸውን ገለጸ ማለት ነው፡፡

3- በመጨረሻም የምንረዳው የአሁኑ ወንጌል ከትክክለኛው የኢንጂል ትምህርት የተቃረኑ አመለካከቶችን እንደያዘና እነዚህ ትምህርቶች

ደግሞ መጤ የብረዛ ውጤቶች መሆናቸውን ነው::

✔ 4- ማስረጃ ከነብዩ ሙሀመድ (ሰዐወ) ንግግር /ሀዲስ/

እንደሚታወቀው ከቁርዓን በመቀጠል አበይት ኢስላማዊ አስተምህሮ ምንጭ ሀዲስ ሲሆን አላህ (ሱወ) እራሱ በተከበረው ቃሉ ከሱ መረጃን ይወሰድ ዘንድ ስልጣን ሰጥቶታል (ቁርዓን 3፡164 እንዲሁም 16፡44)

ከዚህ በታች ጥቂት ሰሂህ (አስተማማኝ) ሀዲሶችን በማስቀመጥ ሀሳቡን ለመፈተሽ እንክራለን

✔ 4.1 ማስረጃ 1

የመጀመሪያው ሀዲስ አልሀኪም አልሙስተድረክ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እንግሊዝኛው እንዲህ ይነበባል

Abu Abdullah Muhammad Ibn Abdullah As-Saffar told us: Ahmad Ibn Mahdi Ibn Rustum Al-Asfahani told us: Mu'azh Ibn Hisham Ad-Distwani told us: my father told me: Al-Qasim Ibn 'Awf Ash-Shaybani told me: Mu'azh Ibn Jabal - radiya Allahu 'anhu - told us that he went to Sham and saw the Christians prostrate to their Bishops and priests and saw the Jews prostrate to their Rabbis and scholars. He said, "Why do you do this?" they answered, "This is the greeting of Prophets (peace be upon him)". I said, "We better do this to our Prophet". Allah's Prophet - salla Allahu 'alaihi wa sallam - said, "#They #lied about their Prophets just as they #distorted #their #Book.

ታሪኩ በአጭሩ በአንድ ወቅት ሙዓዝ ኢብን ጀበል ወደ ሻም ባቀናበት ወቅት ክርስቲያኖችና አይሁዶች ለቀሳውስቶቻቸው ሲሰግዱ በማየቱ ስለ ጉዳዩ ሲጠይቃቸው «ይህ የኑብያት ሰላምታ ነው» ብለው እንደመለሱለትና የአላህ መልእክተኛ ሀሳቡን ሲሰሙ እንዲህ ማለታቸውን ይገልጻል፡፡

« በነብያቶቻቸው ላይ ዋሹ.! ልክ መጽህቶቻቸውን እንደበረዙት» ሙስነድ አህመድ ጥራዝ 4 ገጽ 381 በተጨማሪም አጦበራኒ አልሙዓጀም አልከቢር ጥራዝ 8 ገጽ 31 በተመሳሳይ ይህ ሀዲስ በኢብን ሀጀር አል ሀይተሚ «መጅመዓ ዛዋዲ» ጥራዝ 4 ገጽ 312 ሰሂህ ተብሏል፡፡

በዚህ ሀዲስ በግልጽ እንደምንመለከተው አይሁዶችና ክርስቲያኖች መጽህፍቶቻቸውን ይበርዙ ነበር ከዚህም በተጨማሪ በመለኮታዊ ትእዛዝ ያላገኟቸውን መጤ መመሪያዎች ሳይቀር እየቀጠፉ ያስተምሩ ነበር፡፡

ይህንን ሀዲስ ይበልጥ የአላህ መልዕክተኛ በሌላ ቦታ እንዲህ ያብራሩልናል

«በኒ እስራኢሎች የራሳቸውን መጽሀፍ ጽፈው አሱን መከተል ጀመሩ ተውራትንም ተውት» (ሀዲሱ በአልጦበራኒ አል ሙዓጀም አል አውሰጥ የተዘገበ ሲሆን ሸይኽ ነስሩዲን አልባኒ በሲልሲላ አልሀዲስ አሰሂህ ሀዲስ ቁጥር 2832 ሀዲሱን ሰሂህ ብለውታል።

በሌላ ቦታም የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ይላሉ

«በኒ እራኤሎች በጊዜያት ሂደት ልቦቻቸው ደረቁ ከራሳቸውም መጽሀፍትን መፈጣጠር ጀመሩ» በይሀቂ ሹዑቡል ኢማን ጥራዝ 2 ቁጥር 439 ይህንን ሀዲስ ሸይኽ ነስሩዲን አልባኒ በሲልሲላ አልሀዲስ አሰሂህ ሀዲስ ቁጥር 2694 ላይ ሀዲሱን ሰሂህ ብለውታል።

✔ 2. ማስረጃ 2

የኢይሁዳውያን መጽሀፍ (ብሉይ ኪዳን) በሂደት እንደተበረዘ ይህ ሀዲስ በሚከተለው መልኩ ይነግረናል፡፡

ታሪኩ እንዱህ ነው

ኢይሁዳውያን ዝሙት የፈጸሙ ወንድና ሴትን ፍርድ ይሰጧቸው ዘንድ ወደ ረሱል (ሰዐወ) ዘንድ መጡ፡፡ እሳቸውም ከነሱ ውስጥ ጥልቅ የኦሪት እውቀት ያለውን ሰው እንዲያመጡላቸው አዘዙ ሰዎችም በተባለው መሰረት ይዘው መጡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰዐወ) ዝሙት የፈጸመ ሰው በእነሱ ህግ ቅጣቱ ምን እንደሆነ ጠየቋቸው እነሱም አራት ክስተቱ ሲፈጸም ያስተዋሉ ሰዎች ቀርበው ከመሰከሩ ዝሙተኞቹ ይወገራሉ አሉ፡፡ እሳቸውም ታዲያ ይህንን ህግ ከመተግበር ምን እንዳቆማቸው ሲጠይቋቸው ንግስናቸው እንደተገፈፈና በተጨማሪም ግድያን እንደሚጠሉ ተናገሩ፡፡ ሙሉ ሀዲሱ ሱነን አቢ ዳወድ ሀዲስ ቁጥር 3862 ላይ ይኛል ሸይኽ አልባኒ በሱነን አቡዳውድ 4452 ላይ ያለውን ተመሳሳይ ሀዲስ መሰረት አድረገው ሀዲሱ ሰሂህ ነው ብለዋል፡፡

አሁን እናስተውል ይህ ህግ በኡሪት ውስጥ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 20 ቁጥር 10 ላይ ይገኛል። ነገር ግን አንቀጹ ዝሙተኞቹ መወገር እንዳለባቸው ይገልጻል እንጅ ስለዒይን ምስክሮች አያወራም። ስለዚህም በኑበዩ ጊዜ የነበረውና የአይሁድ ሊቃውንት ያብራሩት የዒይን ምስክር ጉዳይ አሁን ላይ የለም። ይህ ክስተት ብቻውን ኡሪት ጊዜያትን የጠበቀ መሻሻሎች እንዳሳለፈ ማሳያ ነው።

ተጨማሪ

Do you bear witness that I am the Messenger of Allah? He said: No. The Prophet peace be upon him said: Do you read the Torah? He replied back: Yes. Then the Prophet peace be upon him asked: and the Gospel? The man replied: Yes. The Prophet peace be upon him then asked: The Qur'an? The man replied back: No. The Prophet peace be upon him replied back: By He Whose Hand my soul lies, if I willed I would read it. Then the Prophet peace be upon him pulled the

man and asked: Don't you find me in the Torah and Gospel? The man replied back and said: We #find someone who is similar to you and your Ummah (community) and from the place where you were brought up and we were hoping that you would be from amongst us. When you rose up (as a Prophet) we were afraid that it would be you. However, we looked and saw that it wasn't you. The Prophet peace be upon him replied back asking: Why is that? The man said: From him will be 70,000 of his followers from his community who will have no judgment passed on them nor punishment but you have a simple number of men following you. The Prophet peace be upon him replied back: By He Whose Hand my soul lies it is me and it is referring to my Ummah (community). And they are more than 70 thousand, 70 thousand, 70 thousand

በዚህ ሀዲስ የተገለጸውና 70000 ተከታዮች ያሉት ነብይ በአሁኑ ወንጌልና አሪት ውስጥ

አናገኘውም ነገር ግን በኑበዩ ጊዜ በነበረው አሪትና ወንጌል ውስጥ እንደተጠቀሰ ሀዲሱ በማያሻማ መልኩ ያስረዳናል፡፡ በዚህም የምንገነዘበው ቁምነገር እነዚህ መለኮታዊ መጽሀፍት በጊዜያት ሂደት የመሻሻልና የመበረዝ እክል እንዳጋጠማቸው ነው፡፡(ሀዲሱ ሸይኽ አልባኒ በሰሂህ አል ሙዋሪድ ሀዲስ ቁጥር 1765 ሰሂሂ ብለውታል)፡፡

✔ 5- ከኑበዩ (ሰዐወ) ባልደረባዎች ንግግር

✔ 5.1 ኢብን አባስ

ኢብን አባስ በተለያዩ ሀዲሶች መልእክተኛው (ሰዐወ) እውቀቱን የመሰከሩለት ድንቅ ሰሀባ ነበር፡፡ ለአብነትም በሰሂህ አልቡኻሪ ጥራዝ 1 መጽሀፍ 4 ቁጥር 145 ኢብኑ አባስን አላህ ጥልቅ ኢስላማዊ እውቀት ይሰጠው ዘንድ ዱዓ (ጸሎት) ሲያደርጉለት እንመለከታለን፡፡ በተመሳሳይ ጥራዝ 5 መጽሀፍ 57 ቁጥር 100 መመልከት ይቻላል፡፡

እንዲሁም በሰሂህ ሙስሊም 6055 ተመሳሳይ ዱዓ እንዳደረጉለት ተዘግቧል፡፡

ስለ እሱ ለመግቢያ ይህንን ካልን ኢብን አባስ ከመምህሩ (ከኑበዩ) በተማረው መሰረት ምን እንደሚለን እድሉን እንስጠው

በሰሂህ አለቡኻሪ ጥራዝ 9 መጽሀፍ 93 ሀዲስ ቁጥር 613 እና 614 ላይ በግልጽ ቀደምት መለኮታዊ መጽሀፍት እንደተበረዙ ይነግረናል፡፡ ለአብነት 614ን እንመልከት እንግሊዝኛው ትርጉም እንዲህ ይላል፡-

'Abdullah bin 'Abbaas said, "O the group of Muslims! How can you ask the people of the Scripturesabout anything while your Book which Allah has revealed to your Prophet contains the most recent news from Allah and is pure and not distorted? Allah has told you that the #people of the #Scriptures have changed some of Allah's #Books and #distorted it and wrote something with their #own

#hands and said, 'This is from Allah, so as to have a minor gain for it. Won't the knowledge that has come to you stop you from asking them? No, by Allah, we have never seen a man from them asking you about that (the Book Al-Qur'an) which has been revealed to you.>>

በዚህ ሀዲስ ግልጽ በሆነ መልኩ ኢብን አባስ የመጽሀፉ ሰዎች መጽሀፎቻቸውን ይበርዙ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ኢብን ሀዝም ይህን ሀዲስ መሰረት አድርገው ሲናገሩ

«ይህ የኢብን አባስ ዘገባ የሁላችንም እይታ ነው፤ በዚህ ጉዳይ ላይ በኑበዩ (ሰዐወ) ባልደረቦች መካከል ልዩነት አልነበረም፡፡» ኢብን ሀዝም አል ፈስል ፊል ሚላል ጥራዝ 2 ገጽ 3

በተጨማሪም

(Therefore woe) severe punishment, and it is said this means: a valley in Hell (be unto those who write the Scripture with their hands) change the description and traits of Muhammad (pbuh) in the Book (and then say, " This is) in the Book that has come (from Allah " , that they may purchase) through changing and altering it (a small gain therewith) a small gain in terms of means of subsistence and surplus of property. (Woe unto them) theirs is a severe punishment (for what their hands have written) have altered (and woe unto them) and theirs is a severe punishment (for what they earn thereby) of unlawful earnings and bribes. (ተንዊር አል መቅባስ ሚን ተፍሲር ኢብን አባስ ለ2፡79 የተሰጠ ማብራሪያ- የእንግሊዝኛው ቅጅ)

በተመሳሳይ የአል ማዋራዲ አኑኸቱ ወል ዒዩን ለ2፡79 የተሰጠውን ማብራሪያ ስንመለከት ይህን የኢብን አባስን አቋም አስቀምጦ ይተነትናል፡፡

ኢብን ጀሪር አጦበሪ ጃሚዑል በያን ፊ ተዕዊሊል ቁርዓን ለ2፡42 የተሰጠ ማብራሪያ

ነሳኢ 5305 (ሸይኽ ነስሩዲን አልባኒ በ5400 የነሳኢ ሀዲስ ይህም ሀዲስ ሰሂህ መሆኑን ገልጸዋል)

✔ 5.2 የሶስተኛው ኸሊፋ ኡስማን ኢብን አፋን (ረዐ) እይታ (በ34 ዓ.ሂ የሞቱ)

ኢብን ከሲር ኡስማን ኢብን አፋን እንዲህ ማለቱን ዘግበዋል

"Because they (the Jews) #distorted the #Torah. They #added to it what they liked and #erased from it what they hated and they erased the name of Muhammad peace be upon him from the Torah and for that Allah became angry" (ኢብኑ ከሲር ለ2፡79 የሰጡት ማብራሪያ እንግሊዝኛው ቅጅ)

የኡስማን (ረዐ) ንግግር ምንም ማብራራት የሚያስፈልገው አይደለም በግልጽ አይሁዶች ከመጽሀፉ ውስጥ ያሻቸውን ይሰርዙና ያሻቸውን ይጨምሩ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡

✔ 5.3 የሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብነል ኸጣብ (ረዐ) ገጠመኝ

ዑመር (ረዐ) በመሪነታቸው ወቅት ያጋጠማቸው ገጠመኝ ለዚህ የተውራት መበረዝ አጀንዳ አብይ ማሳያ ነው፡፡ አል ሙንዚር አተርጊብ ወተርሂብ በተሰኘው መጽሀፋቸው ጥራዝ 3 ገጽ 188 ታሪኩን ሰሂህ በሆነ ዘገባ ኢንዲህ አስቀምጠውታል፡፡ እንግሊዝኛው እንደሚከተለው ይነበባል

Sa'eed ibn Al Museeb narrated that it happened that a Muslim and a Jew had a dispute so they went to Umar bin Al-Khattab to judge between them. Umar bin Al-khattab ruled in favor for the Jew, which upon the Jew said: "I swear by

Allah, you have judged with the Truth". Umar bin Al-khattab hit the man with a stick that has a small ball on the top of it when he heard him saying that. Then Umar bin Al-khattab asked the Jew, "How do you know that I judged with the truth?" The Jew replied, "#We #find in the #Torah that whoever judges according to the truth two angels from his right and left sides assist him to find the truth. Yet, if he went astray from the truth, they will leave him.

በዚህ ዘገባ ውስጥ የምንመለከተው የወጣቱ ንግግር በአሁኑ ኦሪት ውስጥ አናገኘውም ይህም በተመሳሳይ ሁኔታ ኦሪት ያሳለፈውን የመበረዝና የመለወጥ ሂደት የሚጠቁም ነው።

✔ ማጣቀሻዎች /References/

1- አረጊብ አለኢስፈሂኒ፣ አልሙፋራዳት ፊ ገሪቢል ቁርዓን ጥራዝ 1 ገጽ 122)

2- አሸህራስታኒ ጥራዝ 3 ገጽ 11)

3- እቅቲዳአ ሲራጠል ሙስተቂም ሙኻለፊት አስሀበል ጃሂም ገጽ

4- Shaikh ul-Islaam Ibn Taymiyyah, Creed of Hamawiyyah - Chapter 3: The Way of Ahl us-Sunnah Concerning Allaah's Attributes

5- አል ሙንተቃ ሸርህ ሙወጣዕ ማሊክ፣ ኪታብ አል ጃሚዕ ባብ ማጃዕ ፊ አሰላም አለል የሁዲ ወነስራኒ ለሀዲስ ቁጥር 1514 የተሠጠ ማብራሪያ

6- (http://therefinersfire.org/talmud_proves_messiah.htm+jews+claim+the+talmud+is+from+god&hl=en&ct=clnk&cd=10&gl=ae)

7- ሙስነድ አህመድ ጥራዝ 4 ገጽ 381

8- አጦበራኒ አልሙዓጀም አልከቢር ጥራዝ 8 ገጽ 31

9- መጅመዓ ዛዋዲ ጥራዝ 4 ገጽ 312

10- አልጦበራኒ አል ሙዓጀም አል አውሰጥ

ሸይኽ ነስሩዲን አልባኒ - ሲልሲላ አልሀዲስ አሰሂህ ሀዲስ ቁጥር 2832

11- በይሀቂ ሹዑቡል ኢማን ጥራዝ 2 ቁጥር 439

12- ሸይኽ ኸሩዲን አልባኒ - ሲልሲላ አልሀዲስ አሰሂህ ሀዲስ ቁጥር 2694

13- ሱነን አቡዳውድ 4452

14- ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 20 ቁጥር 10

15- ሸይኽ አልባኒ ሰሂህ አል ሙዋሪድ ሀዲስ ቁጥር 1765

16- ቡኻሪ ጥራዝ 1 መጽሀፍ 4 ቁጥር 145 (እንግሊዝኛው)

17-ቡኻሪ ጥራዝ 5 መጽሀፍ 57 ቁጥር 100 (እንግሊዝኛው)

18- በሰሂህ ሙስሊም 6055

19- በሰሂህ አል ቡኻሪ ጥራዝ 9 መጽሀፍ 93 ሀዲስ ቁጥር 613

20- በሰሂህ አል ቡኻሪ ጥራዝ 9 መጽሀፍ 93 ሀዲስ ቁጥር 614

21- ኢብን ሀዝም - አል ፈስል ፊል ሚላል ጥራዝ 2 ገጽ 3

22- ተንዊር አል መቅባስ ሚን ተፍሲር ኢብን አባስ ለ2፡79 የተሰጠ ማብራሪያ- (የእንግሊዝኛው ቅጅ)

23- አል ማዋሪዲ - አኑኽቱ ወል ዒዩን ለ2፡79 የተሰጠውን ማብራሪያ

24- ኢብን ጀሪር አጦበሪ ጃሚዑል በያን ፊ ተዕዊሊል ቁርዓን ለ2፡42 የተሰጠ ማብራሪያ

25- ነሳኢ 5305

26- አል ሙንዚር - አተርጊብ ወተርሂብ ጥራዝ 3 ገጽ 188

★★★